ኢየሱስ ማነው? ኢየሱስ እንዲት ያድናል?

 **3** ዓመታት በፊት በ መንፈሳዊ በ ስም-አልባ የተጠየቀ

?? ?? ????

3 መልሶች

+ -

0 ድምጾች

ሰላም ወንድማችን/እህታችን

ስለ ኢየሱስ አዳኝነት መሠረታዊ መረዳት ለማግኘት እዚህ በመጫን እንድታነብብ/ቢ እንጋብዝሃለን/ሻለን።

የጌታ ጸጋ ይብዛልህ/ሽ!

 **3** ዓመታት በፊት በ iyesus (7,290 ነጥቦች) የተመለሰ

?? ?? ???? ??? ? ??? ? ? ?

+ -

0 ድምጾች

እየሱስ ማን ነው ለሚለው በአጭሩ የብሉይ ኪዳን አምላክ የአብረሃም የይሳቅ የያኢቆብ አምላክ ጀሆቫ ነው *ሐዋ.22:14:- እርሱም አለኝ። የአባቶቻችን አምላክ ፈቃዱን ታውቅ ዘንድና ጻድቁን ታይ ዘንድ ከአፉም ድምፅን ትሰማ ዘንድ አስቀድሞ መርጦሃል*

ከጥንት የነበረው ነው ወይም የመጀመሪያው ነው
ዮሐ.1:9:- ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ብርሃን ወደ ዓለም ይመጣ ነበር። በዓለም ነበረ፥ ዓለሙም በእርሱ ሆነ፥

' አልፋ'ነው የህያው የእግዚአብሄር ልጅ ነው
ዮሐ.6:69:- እኛስ አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ አምነናል አውቀናልም ብሎ መለሰለት።
ኢስከ አለም ፍጻሜ ድረስ በመካከላችን ያለ ነው
ማቴ.28:19:- -20 ...እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።

እንዴት ያድናል ?
ሃትያት ይቅር ለማለት የምችል ባለ ስልጣን እሱ እንደሆነ ካመንክ *1 ዮሐ.1:9:- በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።*

.....
በተጨማሪም ከላይ ያለው ልንክ በጣም ተቃሚ ነው

 **3 ዓመታት** በፊት በ ስም-አልባ [የተመለሰ]

?? ?? ???? ??? ? ??? ?? ? ?

ኢየሱስ በእንድ አምላክ ፈቃድ በዙ ተዓምራትን ሰርቷል ። አምላክ ግን አይመስለኝም

 2 ዓመታት በፊት በ [አደራ] [አስተያየት ተሰጥቶበታል]

?? ?? ????

የዮሐንስ ወንጌል 1
1 በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር (አብ) ዘንድ ነበረ። ቃልም (ክርስቶስ) እግዚአብሔር ነበረ።
2 ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር (በመንፈስ ቅዱስ) ዘንድ ነበረ።
3 ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም። (ክርስቶስ የሁሉ ፈጣሪ ነው።)
4 በእርሱ ሕይወት ነበረች፥ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች።

እንግዲህ የእግዚአብሔር ቃል ኢየሱስ እውነተኛ አምላክ (ፈጣሪ) መሆኑን ያረጋግጣል።

1 ኛ የዮሐንስ መልእክት 5
20 የእግዚአብሔርም ልጅ እንደ መጣ፥ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደ ሰጠን እናውቃለን፤ እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፥ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው።

 1 ዓመት በፊት በ ስም-አልባ [አስተያየት ተሰጥቶበታል]

?? ?? ????

+ -

0 ድምጾች

ወንድሜ ሆይ፣ (እህት ከሆንሽ ላንቺም ነው፤ ከይቅርታ ጋር።)
ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለህ እምነት እንዲሁ በቀላሉ የሚታይ ጉዳይ አይደለም።

ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገራቸው ቃላት እጅግ ታላቅ ዋጋ ያላቸው እና የዘላለም እድልህን ሊወስኑ የሚችሉ ናቸው። ለምሳሌ እንዲህ ሲል ጌታ ተናግሯል።

የዮሐንስ ወንጌል 6
46 ***አብን ያየ ማንም የለም፤ ከእግዚአብሔር ከሆነ በቀር፥ እርሱ (ክርስቶስ) አብን አይቶአል።***
47 ***እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው።***
48 ***የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ።***

እንግዲህ ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ መምህር መሆኑን እና ፈጽሞ የማይዋሽ መሆኑን አንተም ሆነ ማንም የሚያውቀው ሃቅ ነው። ታዲያ እርሱ በርግጥ "*በእኔ የሚያምን የዘለለም ሕይወት አለው። የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ።*" ብሎ ከሆነ፣ ይህ የማይቀለበስ እና የማይታጠፍ እውነት ነው ማለት ነው።

እና ምን ይመስልሃል? በእርሱ ባለማመንህ እስከ መቼ ልትቀጥል ነው? ያው ሞት አይቀሬ ነውና ባለማመን ውስጥ እያለህ ድንገት ብትሞት የዘላለም ዕድልህ የት ይሆናል?

ድንገት ለፍርድ ቀርበህ፣ በአምላክ ፊት ቆመህ ራስህን ስታገኝ እና ያም ፈራጅና ሁሉን ቻይ አምላክ ራሱ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆኖ ስታገኘው ምን ይውጥሃል? ስለዚህ ዛሬ ገና የምህረት ጊዜ ሳለ፣ አስብበት፤ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በጥልቅ አስበህ ወይ ልታምን ወይ ላታምን ቁርጥ ሃሳብ አድርግና የዘላለም ዕድልህን ወስን።

ለውሳኔህ እንዲረዳህ ግን እኔም ጌታ ያለውን ደግሜ እልሃለሁ፦ **እውነት እውነት እልሃለሁ፤ በእርሱ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው። የሕይወት እንጀራ ኢየሱስ ነው።**

ለምሳሌ እኔ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላኬ እና አዳኜ መሆኑን አምናለሁ። ያመንኩትም ያለመረጃ አይደለም። መጽሃፍ ቅዱስን መርምሬ፣ አሳማኝ ማስረጃ ስላገኘሁ ነው። ያም ብቻ አይደለም። ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ልባዊ እና ግላዊ የሆነ የአባት እና የልጅ ግኑኝነት አለኝ። በእርሱ በማመኔ የዘላለም ህይወት እንዳለኝ አሁኑኑ እርግጠኛ ሆኜአለሁ።

ሌሎች ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገራቸው ቃላትንም ልብ በል። ((ኢየሱስ ስለ ራሱ ሲናገር በሶስተኛ መደብ "እርሱ" እያለ ይናገራል። ይህ ግልጽ እንዲሆንልህ በቅንፍ ውስጥ (ክርስቶስ) የሚል አስቀምጬልሃለሁ።))

የዮሐንስ ወንጌል 3
16 በእርሱ (በክርስቶስ) የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።

የዮሐንስ ወንጌል 3
18 በእርሱ(በክርስቶስ) በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል።

ለመሆኑ እንዲህ በሙሉ ስልጣን የሚናገረው ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ማን ነው ብለህ ብትጠይቅ ***እርሱ እግዚአብሔር ነው።*** ይህንም መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጥልሃል። ከብዙ በጥቂቱ ለማየት፦

ነቢዩ ዳዊት በመዝሙር 23 ላይ
1 እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም።
2 በለመለመ መስክ ያሳድረኛል በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል።
3 ነፍሴን መለሳት፥ ስለ ስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ። ሲል ዘመረ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር የዮሐንስ ወንጌል 10 ላይ፡

11 [b]*መልካም እረኛ እኔ ነኝ።*[/b]
14-15 ***መልካም እረኛ እኔ ነኝ፥ አብም እንደሚያውቀኝ፣ እኔም አብን እንደማውቀው የራሴን በጎች አውቃለሁ፤ የራሴም በጎች ያውቁኛል።***
27 ***በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፤ እኔም አውቃቸዋለሁ፤ ይከተሉኛማል፤***
28 ***እኔም የዘለለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘለለምም አይጠፉም፥ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም።***
29 ***የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፥ ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም።***
30 ***እኔና አብ አንድ ነን።*** " ብሎአል።

እንግዲህ መልካሙን እረኛ፣ ታማኙን የነፍስህን ጠባቂ እንድታምነው እና በስሙ አምነህ የዘላለም ህይወት እንድታገኝ ስለ አንተ አምላኬን እለምነዋለሁ። የአምላክ ጸጋ እና ሰላም ይብዛልህ፤ አሜን።